የኮቪድ-19 የሙከራ መረጃ

SNOHOMISH HEALTH DISTRICT
WWW.SNOHD.ORG

አማርኛ - Amharic

የሙከራ ውጤትዎን በሚጠብቁበት ጊዜ

ይደውሉ

አሰሪውን ወይም የጤና ባለሙያው ኮቪድ-19 እንደተመረመሩ እና የተመረመሩበትን ቀን ያሳውቁ፡፡



ይሸፍኑ

ሳሎን ይሸፍኑ እና ያስነጥሱ ፡ ፡ ዓይኖችዎን ፣ አፍንጫዎን እና አፍዎን ከመንካት ይቆጠቡ ፡፡

በቤትዎ ይቆዩ

ውጤትዎ እስኪ ደርስ ድረስ በቤትዎ ይቆዩ፡፡ ጠያቂ አያስገቡ ወይም ህዝብ በሚሰበሰብበት ወይም የግል ቦታ አይሂዱ፡፡ ለህክምና ካልሆነ በስተቀር ከቤትዎ አይውጡ፡፡

ንፅህ

እጅን በሳሙና እና በውሀ ቢያንስ ለ20 ሴኮንዶች ይታጠቡ፡፡ ሳሙና እና ውሀ ከሌለ ሳኒታይዘር (ቢያንስ 60% አልኮል) ይጠቀሙ፡፡ በጣም ሊነኩ የሚችሉ ቦታዎችን በየቀኑ ያፅዱ፡፡

ምልክትዎን ያስሱ፡

- ምልክቱ የጀመሮትን ቀን ይመዝግቡ ፡፡ እረፍ መውሰድ እና በቂ ፈሳሽ መጠጣት አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ መመሪያው መሰረት ትኩሳትን እና ሳልን ምልክትን የሚቀንሱ መድሀኒቶችን ይውሰዱ፡፡
- የሩሶን የሰውነት የሙቀት መጠን በቀን ሁለቴ ይለኩ፡፡
- የትኩሳት ፣ ሳል እና ተጨማሪ የአተነፋፈስ ምልክቶችን በየቀኑ ይመዝግቡ ፡፡
- የሚያሳስቦት ነገር ካለ ወይም ምክቶቹ ከከፉ ወደ ጤና እንክብካቤ አቅራሚ ይደውሉ ፡፡ ኮቪድ-19 ተመርምረው እንደ ነበረ ይንገሯቸው ፡፡

911 ይደውሉ የሚከተሉት ካጋጠምዎ ወዲያውኑ የህክምና እርዳታ፡

- ከባድ የመተንፈስ ችግር
- ቀለሙ የተለወጠ ከንፈር ወይም ፊት
- ደረቶ ላይ የማያቋርጥ ህመም ወይም ግፊት
- ከባድ የማያቋርጥ ማዞር ወይም ጭንቅላ የመቅለል ስሜት
- ግራ የመጋባት መሆን
- ለመነሳት መቸገር
- የማይሰማ ንግግር (አዲስ ወይም እየባሰ የሄደ)
- አዲስ የሚጥል በሽታ ወይም የማያቆም የሚጥል በሽታ

በቤት ለመቆየት ምን ያህል ጊዜ (ባዶ ቦታዎችን ይሙሉ)

የህመም ስሜት የተሰማኝ ቀንን	ከ10 ቀናት በኋላ ያለው ቀንን	ትኩሳቱ ቀጥሎ ነበርን	ከ24 ሰአት በኋላ ያለው ቀንን	ምልክቶቹ ጥሩ ሆኑን	የቅርብ ጊዜውን ያክብሩ እና ከስር ይፃፉት፡፡ **እስከዚያ ድረስ በቤትዎ ይቆዩን**

ከ **ወአ ደኘ**H 820-089 ተስተካክሏል

ስለ መድህን ክፍያ

- የጤና መድህ ቢኖሮትም ፣ ለሙከራ የሚከፍሉ ሲሆን ደረሰኝ አይደርሶትም ፡፡ የጤና መድህን ካሎት፣ **ጠወ** መድሀኒት የግል የጤና መድህኖን፣ ሜዲኬድ፣ እና ሜዲኬርዎን ይይዝሎታል፡፡ የጤና መድህን ከሌሎት፣ **ጠወ** ሜድስን ለምርመራዎ ወጪ በቀጥታ ከፌዴራል መድህን ለሌላቸው የኮቪድ የምርመራ ተመላሽ ገንዘብ ይፈልግሎታል፡፡ ከገንዘብ ነፃ የሆነ ምርመራ ለእርሶ ለማቅረብ ከግል መድህን፣ሜዲኬድ እና ሜዲኬር ከፌዴራል መድህን ለሌላቸው ተመላሽ ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
- የበለጠ ይማሩ**ን ህትትፕስን//ውውው.ስንኝህድ.ኝርግ/ትዥስትጽንግ**

Rev. 09/16/21

(ከጀርባ የቀጠለ)

የእርሶ ምርመራ ውጤትዎ ምንድነው?

ፖዘቲቭ

ምልክቶች አለዎት?

አዎ

ምልክቶቹ ከታዩ ጀምሮ 10 ቀን እስኪያልፍ ድረስ እና ለ24 ሰዓታት ከትኩሳት ነጻ እስኪሆኑ እና ምልክቶቹ እስኪሻሉ ድረስ እቤትዎ ራስዎን ለይተው ያቆዩ::

አይደለም

ከምርመራ ቀን በኋላ እስከ 10 ቀናት ራሶን በቤትዎ ያግሉ

ኔገቲቭ

ከተረጋገጠ ኬዝ ጋር ቅርብ ግንኙነት አልዎት?

አዎ

ሙሉ ለሙሉ ክትባቱን ከተከተቡ‹* ፣ እንዲሁም ምንም አይነት የህመም ምልክት ካላሳዩ ራስዎን ለይተው ማቆየት አይጠበቅቦትም፤ ነገር ግን የህመም ምልክቶችን ካዳበሩ ራስዎን ለይተው ማቆየት ይኖርቦታል:: ክትባቱን ካልወሰዱ ግን ለ14 ቀናት ራስዎን ለይተው ማቆየት ይኖርቦታል:: የህመም ምልክቶችን ካዳበሩ ባስቸኳይ ለዶክተርዎ ይደውሉ::

አይደለም

ለ24 ሰዓታት ከትኩሳት ነጻ ከሆኑ በኋላ እና ምልክቶቹ መሻሻል ሲጀምሩ እንቅስቃሴዎችዎን እንዳገና ይጀምሩ::

---

* ሙሉ ለሙሉ ክትባቱን አጠናቀቁ የሚባለው የክትባቱን የመጨረሻ ከወሰዱ ከ2 ሳምንታት በኋላ ነው (ለምሳሌ የ ’Pfizer’ ወይም የ ‘Moderna’ ሁለተኛ ውስዶ ከወሰዱ፣ ወይም የ ‘Johnson & Johnson’ ብቸኛ ውስዶ ከወሰዱ ከ2 ሳምንታት በኋላ)::

ኮቪድ-19 ተመርምረው ፖዘቲቭ ከሆኑ

- በቤትዎ ለተፈለገው ጊዜ ያክል እራሶን ማግለሎን ይቀጥሉ::
- እንደ አስፈላጊነቱ ፣ለጤና ባለሙያዎን ወይም ለሰራተኛዎ ኮቪድ-19 ፖዘቲቭ እንደ ሆኑ ያሳውቁ::
- በጤና ዲስትሪክት የሚቀጥሩት እርምጃዎች ምን መሆን እንዳለበት ሊጠሩ ሲሆን፣ በቅርቡ ስለነበሮት ንክኪም ይወያያሉ::
- ምልክትዎ እየከፋ ከሄ፣ እባክዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ወይም 911 በድንገተኛ ይደውሉ::

የምርመራ ወጤትዎን እንዴት ያግኙ

- የምርመራ ውጤትዎ ከ2 እስከ 3 ቀናት ውስጥ ይገኛል::እባክዎ ተመርምረው በትንሹ 3 ቀናት ካልሞላዎ ለላቦራቶሪ ባለሙያ አይደውሉ::

የምርመራ ውጤትዎ ሲደርስ ማስታወቂያ አይደርሶትም:: የምርመራ ውጤትዎን ለማግኘት:

- የ **ቀR** ኮዱን በስልኮ ላይ ያለውን ካሜራ መተግበሪያ ስካን በማድረግ በቀጥታ ውጤትዎን ያግኙ ወይም፣
- ወዳ **ኀ ሀትትፐስኀ//ስኸችጥርኸልጽንክ.ልእብምኸድ.ጥው.ኸድጥ** በመሄድ 16 ዲጂት ኮዶን እና የልደት ቀኖን ከስር በማስገባት ይመልከቱ:: የምርመራ ውጤትዎን ለማየት ተመርምረው በትንሹ ሁለት ቀን ካለፈ በኋላ እንዲያረጋግጡ እንበረታታዎታለን::
- **ቀR** ኮዶዎ ከጠፋቦት ወይም ደግሞ የምርመራ ውጤትዎን ለማግኘት ከተቸገሩ፣ ወደ **ጠንጽሽኸርስጽትይ ኝፍ ወእስሀ–ጽንግትኝን ልእብኝርእትኝርይ** የአገልግሎት መስመር ላይ ለቴክኒካል እገዛ በ 1-833-562-1212 ይደውሉ::

ለድንገተኛ የህክምና ፣ 911 በመደወል እናም የተላኩትን ሰራተኞች ኮቪድ-19 ይዘት ሊሆን እንደሚችል ያሳውቁ::

ለበለጠ መረጃኀ ወወወ.ሰነኝዘደ.ኝRገ/Cኝሽፗደ ይጎብኙ